የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

**ከኢሰመጉ የተሰጠ አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ**

# መንግስት በአድዋ ድል በዓል በተፈጠረው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ኃላፊነት ሊወስድ ይገባል!!!

የካቲት 25/2015 ዓ.ም

## መግቢያ

ኢሰመጉ በየካቲት 23/20215ዓ.ም በተከበረው የአደዋ ድል በዓል ወቅት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከህብረተሰቡ የሚደርሱ ጥቆማዎችንና መረጃዎችን መነሻ በማድረግና ባለሞያዎችን በመመደብ ሁኔታዎችን ሲከታተል ቆይቷል፡፡

የአድዋ በዓል ለ127ኛ ጊዜ ለማክበር የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እንደወትሮው ለበዓሉ የሚዉሉ የዳግማዊ አፄ ሚኒሊክንና የእቴጌ ጣይቱን ምስል የያዙ ካኒቴሪያዎችን ለማሳተም ከበዓሉ አንድ ሳምንት በፊት ጀምሮ በሸሮ ሜዳ አካባበቢ የአካባቢ ወጣቶችና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደነበርና የመንግስት ፀጥታ ኃይሎች የካኒቴሪያዎቹ ህትመት እንዳይታተም በመከልከል ሱቆችንና ማተሚያ ቤቶችን በማሸግ የፀጥታ ኃይሎች ከህግ አግባብ ውጭ የሆነ ስራ ሲያከናውኑ እንደነበር ኢሰመጉ ካሰባሰበው መረጃ ለመረዳት ችሏል፡፡ በበዓሉ ዋዜማ ወቅት ዜጎች በዓሉን ለማክበር ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት አንዳንድ የፀጥታ አስከባሪዎች ወከባ፣ዘቻና አንዳንድ ተገቢ ያልሆኑ እርምጃዎችን ሲወስዱ እንደነበር ለመረዳት ችለናል፡፡

በየካቲት 23 ቀን 2015ዓ.ም ሕዝቡ 127ኛ የአድዋ ድል በዓልን በሚኒልክ አደባባይ ለማክበር በአካባቢው ለመታደም የሚመጡትን የሰንደቅ ዓላማ ምስል፣ የዳግማዊ አፄ ሚኒሊክንና የእቴጌ ጣይቱን ምስል ያለበትን ልብስ ለብሰው ወደ አደባባዩ እንዳይገቡ በመከልከል ዜጎች መብታቸውን እንዳይጠቀሙ ታግደዋል፡፡ይህም ሳይበቃ የፀጥታ ኃይሎች ህገወጥ የኃይል እርምጃ በመውሰድ የጪስ ቦምብ እና ፕላስቲክ ጥይት በመተኮስና ሕዝቡን በዱላ ጭምር በመደብደብ በዓሉን ለማክበር በታደሙ እንዲሁም በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ታቦት ለማንገስ የወጡ ዜጎች ላይ የሕይወትና የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በርካታ ዜጎችም ከዋዜማው ጀምሮ እንዲታሰሩ መደረጉን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ለመረዳት ችሏል፡፡ በዚህም ተገቢ ያልሆነ እርምጃ ምክንያት የአንድ ሰው ሕይወት ማለፉንና በርካታ ሰዎችም ጉዳት እንደደረሰባቸው ኢሰመጉ ከስፍራው ካሰባሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 3፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም (ICCPR) በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ (ICCPR) የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2)ይደነግጋል።

የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት መብቱ ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14“ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው” ሲል ይደነግጋል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በአንቀጽ 16 ላይ ማ ንም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው ሲል ያስቀምጣል፡፡

የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች (ACHPR) አንቀጽ 6 ላይ ማንኛውም ሰው ነጻነቱና አካላዊ ደህንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው ሲል ይደነግጋል፡፡

**የኢሰመጉ ጥሪ፡**

መንግስት በየጊዜው የአድዋ ድል በዓል ሲከበር እየተፈጠረ ያለውን ውዝግብና ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለመፍታት ተገቢነት ያለውና ማህበረሰቡን ያማከለ ጀግኖች አባቶቻችን ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለማቆየት የከፈሉትን ዋጋ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚጠቅም እርምጃ እንዲወስድ፤

- በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በተተኮሰ የጪስ ቦምብ ምክንያት በንጹሃን ዜጎች ላይ ለደረሰው ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መንግስት ሕዝቡን በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቅ፤
- በቅርቡ በተደጋጋሚነት እየተከሰተ ያለው የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚወስዱት ከመጠን ያለፈ የኃይል እርምጃና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲቆም መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያደርግ፤
- በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች የሕይወትና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች መንግስት ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል፤
- ከሕግ አግባብ ውጭ የታሰሩ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤
- መንግስትና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሀገሪቷ ዘላቂ ሰላም እንዲቀጥልና ሕዝቡ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመራ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ